ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

የስብሰባ ጥሪ

# የባለአክሲዮኖች 23ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 19ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ

**ለተከበራችሁ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማኅበር ባለአክሲዮኖች፡-**

የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 23ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 19ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366፣ 367፣ 370፣ 371 እና 372 መሰረት ሐሙስ **ታህሣሥ 6 ቀን 2015** ዓ.ም. ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ ቦሌ አካባቢ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በአካል ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

- የባንኩ የተፈረመ ካፒታል 10,000,000,000.00
- የባንኩ የተከፈለ ካፒታል 5,000,000,000.00
- የባንኩ የምዝገባ ቁጥር KK/AA/02/0000814/2004
- የባንኩ አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09 ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ህንጻ

## የ23ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፡-

1. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
2. እስከ ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄዱ የአክሲዮን ግዢና ዝውውሮችን መቀበል፣
3. የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ የ2021/22 በጀት ዓመት ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
4. የባንኩን የውጭ ኦዲተሮች የ2021/22 በጀት ዓመት ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዓመታዊ የሥራ ዋጋና ወርሃዊ አበል በሚመለከት በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
6. በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው የዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ምርጫ ማከናወን፣
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ወርሃዊ አበልና የሥራ ዋጋ መወሰን፣
9. የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ፣

## የ19ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፡-

1. የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
2. የባንኩን የመመስረቻ ጽሁፍ በአዲሱ የንግድ ህግ 1143/2013 መሰረት ስለማሻሻል፣
3. የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ማጽደቅ፣

## ማሳሰቢያ፡-

- ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ለመገኘት ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ፣ መንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ዋናውን ከፎቶ ኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡
- በውክልና የሚገኙ ከሆነ የወካዩን ባለአክሲዮን ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን ከኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡
- ውክልና መስጠት የሚፈልግ ባለአክሲዮን **ከህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 5 ቀን 2015 ዓ.ም** ድረስ በስራ ሰዓት ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት ይዞ ሰንጋተራ በሚገኘው የባንኩ አዲሱ ዋና መ/ቤት ህንጻ ምድር ወለል ለዚሁ በተዘጋጀው ቦታ በግንባር በመቅረብ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት መወከል ይቻላል፡፡
- በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ወይም አግባብ ባለው አካል በተሰጠ ውክልና በስብሰባ ላይ የሚገኝ ተወካይ የወካዩን ባለ አክሲዮን ኢትዮጵያዊነት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን ከኮፒ ጋር እና የውክልናውን ዋና ከኮፒ ጋር ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡

**የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ**

9698

ይሠሯል ከልብ፣
እንደ ንብ !
Committed to Service Excellence !